**I** አጠቃላይ መግለጫ

ፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሃብት ልማት ሚኒስቴር የሥራ ዝርዝር መግለጫ ቅጽ

| የመስሪያ ቤቱ ስም | የሥራ መደቡ መጠሪያ | የሥራ ዘርፍ/የሥራ ሂደት |
|---|---|---|
| ጤና ጥበቃ ሚኒስቴር | ቤተሰብ ጤና ፕሮፌሽናል IV | የህብረተሰብ ጤና |
| | | |
| | በፐብሊክ ሰርቪስና የሰው ሀብት ልማት ሚኒስቴር.ቢሮ ብቻ የሚሞላ | |
| የቅርብ ኃላፊ የሥራ መደብ/ተጠሪነት | የሥራው ደረጃ | የሥራው ኮድ |
| | **XIV** | |
| መስሪያ ቤቱ የሚገኝበት ቦታ | | |
| በየደረጃው ባሉ ጤና ተቋማት | | |

**II.** የሥራ መደቡ ዋና ዓላማ፣ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

**2.1.** የሥራ መደቡ ዓላማ፡-

- በጤና ኤክስቴሽን አገልግሎት ላይ ጥናትና መርምር በማካሄድ፣ ፈውስ ሕክምና አገልግሎት ለሕሙማን በምርመራና ሕክምና በማድረግ፣ በተሀድሶ ሕክምና ለአካላዊ ጉዳተኞችና ህሙማን ድጋፍና ክብካቤ በማድረግ፣ በመከላከል ሕክምና ጤናን በማጎልበት እና በሽታን በመከላከል በበሽታ የተጠቁ ህሙማንን እና የድንገተኛ አደጋ ጉዳተኞች ስቅይ መቀነስ፣ ወደ ጤናማ ኑሮአቸው መመለስ፣ ሞትና አካል ጉዳትን በመቀነስ የበሽታን ስርጭት በመከላከል የሕብረተሰቡን ጤና ማሻሻል ነው።

**2.2.** ከሥራ መደቡ የሚጠበቁ ውጤቶችና ተግባራት

ውጤት **1**፡ በጤና ኤክስቴሽን አገልግሎት ላይ ጥናትና መርምር ማካሄድ፣ ምርጥ ተሞክሮ መቀመርየ ማስፋፋት

- በጤና ኤክስቴሽን አገልግሎት ላይ በተለያዩ በጥናትና አስተዳደራዊ ሪፖርት የሕትመት ውጤቶችን በማሰባሰብ ያነባል፣ የፕሮግራሙ የአፈፃፀምና የመሻሻል ማነቆ ከሆኑት መካከል በጥናትና ምርምር መልስ ሊያገኙ የሚችሉ ችግሮች ይለያል፣
- የተለየውን የጥናት ርዕስ ላይ ምርምር ማድረግ ያስፈለገበትና ያለው ፋይዳ ያብራራል፣ በዚህም ከጥናቱ ጋር ተዛማጅ ያላቸውን አለም አቀፋዊና ሀገራዊ የፅሁፍ ውጤቶችን በማሰባሰብ ማብራሪያ ያዘጋጃል፣
- በጥናቱ ርዕስ ላይ ተመስርቶ የጥናት ፕሮፖዛል ያዘጋጃል፣ ጥናቱን ያካሂዳል፣ የጥናት መረጃውን ተመስርቶ ውጤቶችን ያወጣል፣ ትንትና ይሰጣል፣ ትርጉም በመስጠት ማጠቃለያና ምክረ ሀሳብ ይሰጠል፣
- የጥናትና ምርምሩን ምክረ ሀሳብ የተሰጡትን ነጥቦች የጤና ኤክስቴሽን አገልግሎት ሊያሻሽል ወደ ሚያስችል የድርጊት መርሀ ግብር ያዘጋጃል፣ በተለያዩ መድረኮች የማስተዋወቅና የአድቮኬሲ ስራዎችን ይሰራል፣
- የድርጊት መርሀ ግብር በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ ይተገብራል፣ በየወቅቱም ክንውኑንም ይከታተላል፣ የፕሮግራሙ መሻሻል ይገመግማል፣
- በጤና ኤክስቴሽን አገልግሎት የተገኙ ምርጥ ተሞክሮ የሚለይ መስፈርት ያዘጋጃል፣ በመስፈርቱም መስረት ምርጥ ተሞክሮን ይለያል፣ አካባቢያዊ ተስማሚነት ይለውጣል፣ ወደ ሌሎች አካባቢዎችም ያስፋፋል፣ አተገባበሩን ይከታተላል፣ ለውጡንም ይገመግማል፣

ውጤት **2**፡ የጤና ኤክስቴሽን አግልግሎት ማሻሻያ ፕሮጀክት መቅረፅ፣ የቴክኒክና የገንዘብ ድጋፍ ማሰባሰብ፣ በተግባር ላይ ማዋል

- የጥናትና ምርምር ዝክረ ምክርን ለመተግበር፣ ምርጥ ተሞክሮ ለማስፋና በዕቅድ የተያዙ ተግባራት ለመተግበር የታሰቡ የጤና